# የፍቅር ሽማኔ

ፈልቀቅ አደረግሁት ጥጡን ከፍሬው ለየሁት፤
አያያዜንም አሳምሬ እንዝርቱን አሾርኩት፤
ትንሽ በትንሽ እያደረግሁ ጊዜዬን ፈጅቼ ከመርኩት፤
ክምሬንም ቀስ በቀስ እከረጢቴ ሞልቼ ከተትኩት።

ያጋጣሚው ነገር እጅጉን ገረመኝ ደነቀኝ፤
የምወደው ጓዴ የሞላ ከረጢቱን ሰጠኝ፤
ለሽማ የሚበቃ ፈትል ማግኘቴ እጅግ አስደሰተኝ፤
እሱም አስቀድሞ ተረዳድተን ሽማ እንደንሰራ ጠየቀኝ።

ከረጢቶቻችንን ፈተን ክምራችንን ደባልቀን፤
እሱ በአንድ በኩል እኔም በሌላው ተቀመጥን ፤
ወርውረን ተቀባበልን አጠነጠንን ገፋንም አጠበቅን ፤
ሌት ተቀን በመስራት ሽማችንን አሳደግን።

ጥልፍም ጠለፍንበት የበለጠ ውበት እንዲሰጠው፤
ስስ ሆኖም እነዳይቀደድብን ደርሰን ሰፋነው፤
ዘርፏም እንዲያምርልን በፅዳት ቋጨነው፤
ከዚያ ወዲህ ነው እኔና ጓዴ የፍቅር ሽማኔ ሆኔን የቀረነው።

ጥጡ ፍቅሬ ሲሆን እንዝርቱ ሕይወቴ፤
ከረጢቱም ሆኖ ፍቅር መሙያ ቤቴ፤
ሽማውም ወዳጄ ነው እስከ እለተ ሞቴ።

ከ ኒኒ ለገሰ